# የባሕረ ሐሳብ ትምህርት ለዘመን አቆጣጠር፣ ለከዋክብት እና ለአየር ትንበያ ጥናት መጽሐፈ ሄኖክ መነሻ

ዮሐንስ ደምስ በለጠ[121]

## አኅፅሮተ ጽሑፍ

ባሕረ ሐሳብ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት ያለው የቍጥር ትምህርት ነው፡፡ ይኽ ትምህርት የፀሐይን፣ የጨረቃን፣ የክዋከብትንና የነፋሳትን ዑደታቸውንና የቆይታ ጊዜያቸውን ርዝማኔ ለይቶ ይቈጥራል፡፡ በእነዚኽ ዑደቶች አማካኝነት ዘመናትን ለመቍጠር፣ አንዳንድ ያለፉ እና ወደፊት የሚመጡ ክስተቶችን ጊዜያቸውን ለማስላት ይጠቅማል፡፡ የኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር መነሻው ዘመነ ፍጥረት ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማ የባሕረ ሐሳብ ትምህርት መነሻ መጽሐፈ ሄኖክ መኾኑንና ለዘመን አቈጣጠር፣ ለከዋክብት እና ለአየር ትንበያ ጥናት ያለውን ፋይዳ ማሳየት ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የተለያዩ ፍጥረቶችን ለመመራመር የሚጠቀሙበት ዐቢይ መጽሐፍ መጽሐፈ ሄኖክ ነው፡፡ ስለዚኽ መጽሐፈ ሄኖክ የኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር እንዲኹም የባሕረ ሐሳብ ፍልስፍናውና መሠረቱ ከሄኖክ መጽሐፍ የተቀዳ ነው፡፡ ይኽንንም ለማረጋገጥ የተለያዩ የጽሑፍ ማስረጃዎችን በማመሳከር፣ ሊቃውንትን በመጠየቅ ጥናቱ ተከናውኗል። የጥናቱ ውጤት የኢትዮጵውያን የዘመን አቈጣጠር ስልት በፀሐይ፣ በጨረቃና በከዋክብት እንደ አስፈላጊነቱ የሚቈጥር እንደኾነ፤ ባሕረ ሐሳብ ትምህርት በዘመናዊ ሳይንስ ከፍተኛ የሒሳብ ዕውቀት በተለይ "Algebira & Trigonometry" እንዲኹም የምርምር ችሎታ የሚጠይቀውን ትምህርት በቃል ብቻ ያለ ሒሳብ መሥሪያ ማሽን መሥራት እንደሚቻል የሚያሳይ ሀገር በቀል ጥበብ ነው፡፡ በተጨማሪም ቀደም ባሉት ዘመናት ባሕረ ሐሳብ ትምህርት በኢትዮጵያ ውስጥ በነበረው የትምህርት ዘይቤ የነበረውን አጠናን እና የማኅበረሰቡን ከፍተኛ የፍልስፍና ጥበብ በዘመን አቈጣጠር፣ የሰማይን ‹‹ምሥጢር›› ለማወቅ (astronomical studies)፣ ለኮከብ ቈጠራ (astrology)፣ ለአየር ንብረት ትንበያና ስለወቅቶች መፈራረቅ (meteorology and climate studies) ለመሳሰሉት ጉዳዮች የሚያገለግል ጥበብ ነው፡፡

**ቍልፍ ቃላት**:- መጽሐፈ ሄኖክ፣ ባሕረ ሐሳብ፣ አቡ ሻኽር፣ ሥነ-ፈለክ

---

[121] BSC mathematics & Msc Computational and data science, AAU, Email: yohannesd23@gmail.com

# መግቢያ

ጥንታዊዉ የኢትዮጵያ የቊጥር ትምህርት የዘመን አቈጣጠር እና የሥነ-ፈለከ ጥናት ዐጠቃሎ የያዘው ትምህርት ስያሜ በሊቃውንት ዘንድ አከራካሪ ነው፡፡ ለምሳሌ አለቃ ያሬድ ባሕረ ሐሳብ አጽዋማት እና በዓላትን፣ የፀሐይ፣ የጨረቃ፣ የከዋክብት እና ሐሳበ ነፋሳትን አጠቃላይ የያዘውን ባሕረ ሐሳብ ይሉታል፡፡ በሌላ በኩል አባ ገብረሥላሴ ወ/ሚካኤል ደግሞ በዓላት እና አጽዋማት የያዘውን መረጃ መጽሐፍ ብለው ሰይመውታል፡፡ መምህር ስቡሕ አዳምጤ ፣ጌታቸው ኀይሌ እና መሪጌታ ዘነበ ኀየሎም አጽዋማት እና በዓላት ላይ የሚያተኵረውን መጽሐፍ ባሕረ ሐሰብ ብለው ይጠሩታል፡፡ ይኹን እንጂ ይኽ ጥናት ኹሉንም አጠቃሎ የያዘውን የአለቃ ያሬድን ባሕረ ሐሳብ የሚለውን መጠሪያ የሚጠቀም ይኾናል፡፡ ሊቃውንት ጥልቅ የኾነውን የሥነ-ፈለክ ትምህርት ማለትም ሥለ ፀሐይና ጨረቃ ዑደት እና የነፋሳትን ምሥጢር የሚያጠናውን አቡሻኽር እንደኾነ እና የዘመን አቈጣጠር ደግሞ ባሕረ ሐሳብ ብለው የሚከፍሉ እንዳሉ ኹሉ ከስሙ ትርጓሜ በመነሣት ባሕረ ሐሳብ ኹሉን ያዘ ነው የሚሉ ሊቃውንት ደግሞ በርካታ ናቸው፡፡ በመኾኑም ይኽ ጥናት በዋናነት ባሕረ ሐሳብ የሚለውን እንደ አጠቃላይ በመውሰድ የተዘጋጀ ነው፡፡

ከላይ አስቀድሞ ለመግለጽ እንደተሞከረው ባሕረ ሐሳብ፣ ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብትን በመጠቀም እንዲኹም የነፋስን አቅጣጫ በመረዳት፤ ሰዓት፣ ቀን፣ ወርና ዓመትን የመሳሰሉ የጊዜ ርዝመቶችን መለኪያዎች አድርጎ በመከፋፈል፣ ለዚኽም የሚኾን ዘዴ ደንብና ሥርዓት በማዘጋጀት ለሃይማኖታዊም ኾነ ለተቋማዊ ሥራዎች የሚረዳ ዕቅድ ለማዘጋጀት የሚጠቅም ነው፡፡ [122] ይኽም እንደ እርሻ፣ ንግድና ሌሎችም የኅብረተሰብ ጉዳዮችን በሥነ ሥርዓት ለመከወን ያግዛል፡፡ የዘመን አቈጣጠር ሥለ ማኅበራዊ ኑሮ ጠቀሜታና በሃይማኖት ተግባሮችን ለማከናወን በሚያገለግል መልኩ ተፈጥሮአዊዉን የወቅቶች ክፍፍል እርስ በእርሳቸው የሚያመ ቻችበት ዘዴ ነው፡፡ እንዲኹም ዓመት ወስኖ ወደ ትንንሽ ክፍሎች በመከፋፈል እነዚያ ትንንሽ ክፍሎች ደግሞ ስንት ቀኖች እንደሚኖራቸው የመወሰን ደንብ በመኾኑ የሕዝብና የሃይማኖት በዓላት ቀኖችን አስቀድሞ ለማወቅና ዕቅድ ለማውጣት ይረዳል፡፡

[122] ጌታቸው ኃይሌ፡ 1993 ዓ.ም. *ባሕረ-ሐሳብ የዘመን ቆጠራ ቅርሳችን ከታሪክ ማስታወሻ ጋራ፡፡*

የዚኽ ጥናት ዋነኛ ትኩረት መጽሐፈ ሄኖክ ለኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር መነሻ መኾኑን ማጠየቅ ሲኾን፣ ጥናቱ 1980 ዓ.ም በመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ታትሞ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ የዋለውን መጽሐፈ ሄኖክ የሚዳስስ ነው።

# የጽሑፉ አነሳሽ ምክንያት

የዚኽ ጥናት አነሳሽ ምክንያት የኾነው የባሕረ ሐሳብ ትምህርት ምንጬ በተለያዩ ሊቃውንት ዘንድ ያለው የሐሳብ ልዩነት ማጥናት እና የባሕረ ሐሳብ ትምህርት ይዘትን በስፋት ማስገንዘብ ነው። አንዳንድ ምሁራን የኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር መነሻ የኾነው ባሕረ ሐሳብ ትምህርት ምንጩ ከግብፅ እና ከዕብራውያን እንደኾነ[123] በተጨማሪም ከጎርጎርዮሳውያን አቈጣጠር ጋርም አንድ ዓይነት እንደኾነ የሚያስረዱ ሲኾን ይህንን ሐሳብ በመሞገት የዚኽ ጥናት ዋነኛ ጉዳይ የኢትዮጵያ ዘመን መቍጠሪያ ባሕረ ሐሳብ ትምህርት መነሻው መጽሐፈ ሄኖክ እንደኾነ ከላይ የተጠቀሱት ሊቃውንት ሥለ ኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር ካቀረቡት ምንጭ ልዩ መኾኑን ማሳየት ነው። እንዲኹም ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ውስጥ በነበረው የትምህርት ዘይቤ የነበረውን አጠናን (የዘመን አቈጣጠር ጥናት) እና የማኅበረሰቡን ከፍተኛ የፍልስፍና ጥበብ የሚጠቁም ሲኾን ለማኅበራዊ መስተጋብር ያለው ፋይዳ የጎላ እንደኾነ ያሳያል። በተጨማሪም ለሳይንሳዊ ጥናቶች የሕዋ ወይም ሥነ-ፈለክ (cosmos) እና የአየር ንብረት ምርምር ዓላማ የባሕረ ሐሳብ ትምህርት አስፈላጊ መኾኑን ነው።

## የጥናቱ ዓላማ

የጥናቱ ዓላማ የባሕረ ሐሳብ ትምህርት ምንጩ መጽሐፈ ሄኖክ መሆኑን ፣ ለዘመን አቈጣጠር፣ ለከዋክብት እና ለአየር ትንበያ ጥናት ያለውን ፋይዳ ማሳየት ነው። ዝርዝር ዓላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው።

- የባሕረ ሐሳብ ትምህርት ምንጭ መጽሐፈ ሄኖክ መሆኑን ማስተዋወቅ፣
- ባሕረ ሐሳብ ስለከዋክብት እና የነፋሳት ዑደት ለማወቅ የሚያስችል መሆኑን መፈተሽ፣

[123] ጌታቸው ኃይሌ፡ 1993 ዓ.ም. ባሕረ-ሐሳብ የቀመር የሥነ-ፈለክ ምስጢር፡፡

- ጥንታዊ የኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር ምንጩ ባሕረ ሐሳብ መሆኑን በማሳየት ልዩ ልዩ ጠባይዓትን መግለፅ፣

## የጥናቱ አስፈላጊነት

የዚኽ ጥናት አስፈላጊነት የአትዮጵያ ዘመን አቀጣጠር መነሻው አቡሻኽር ሳይኾን መጽሐፈ ሄኖክ እንደኾነ መነሻ ሐሳብ ማቅረብ ነው። የባሕረ ሐሳብ ትምህርት ከመጽሐፈ ሄኖክ አንጻር የሚዳሳስ እና ትምህርቱ ዘመን ከመቍጠር ባሻገር ጥልቅ የኾነ ሒሳባዊ (mathematics) ቀመሮችና የአሠራር ስልቶችን (Algorithms) በቃል የማጥናት[124] ክሂልን ማዳበር የሚያስችል መኾኑን ማሳየት እና የሥነ-ክዋክብት እና የአየር ትንበያ ትምህርት የያዘ መኾኑን ይዳስሳል።

## የጥናቱ ዘዴ

ይኽን ጽሑፍ ለማዘጋጀት አጥኚው አንደኛ እና ኹለተኛ የመረጃ ምንጮችን የተጠቀመ ሲኾን፣ ከሚመለከታቸውን የባሕረ ሐሳብ መምህራን በቃለ መጠይቅ መረጃ ተሰብስቧል። እንዲኹም የሰነድ ፍተሻ እና ከርእሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የሒሳብ (Mathematics) ቀመሮች ለትንተና አገልግሎት ላይ ውለዋል።

## ባሕረ ሐሳብ እና ታሪካዊ ዳራው

ባሕረ ሐሳብ ማለት የቃሉ ትርጉም ቍጥር ያለው ዘመን፣ የዘመን ቍጥር ማለት ነው።[125] ባሕረ ሐሳብ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት ያለው የቍጥር ትምህርት ነው። ይኽ ትምህርት የፀሐይን፣ የጨረቃን፣ የክዋከብትንና የነፋሳትን ዑደታቸውንና የቈይታ ጊዜያቸውን ርዝማኔ ለይቶ ይቆጥራል። በእነዚኽ ዑደቶች አማካኝነት ዘመናትን ለመቍጠር፣ አንዳንድ ያለፉ እና ወደፊት የሚመጡ ክስተቶችን ጊዜያቸውን ለማስላት ያገለግላል።

ባሕረ ሐሳብ ያለፈውን፣ አኹን ያለውንና ወደፊት የሚኾነውን እየቈጠረ በስፍር(በልክ) የሚያስረዳ ነው። ለመጠሪያም የሚጠቀምባቸው በዋናነት የፀሐይን፣ የጨረቃንና የከዋክብትን ዑደታትን ሲኾን እነዚኽን ተጠቅሞ ዘመንን በዓመት፣

[124] በቃል ማጥናት ስንል፡- ጽሑፋዊ ማጣቀሻ ሳይመለከቱ በአእምሮ ክህሎት ብቻ ላይ ተመሥርቶ በቃል የሚደረግ ገለጻና እና ትንታኔ ማለት ነው።

[125] አለቃ ያሬድ ፈንታ፡ 2004 ዓ.ም ባሕረ-ሐሳብ የቀመር የሥነ-ፈለክ ምስጢር።

በወር፣ በቀን፣ በሰዓት፣ ወዘተ. በመከፋፈል ይሰፍራል፡፡ ለዚኽም በተለያየ ጊዜ የሚመላለሱ ዐውዶች ዘመንን ለመለየት (ለመቍጠር) ይጠቅማሉ፡፡

የኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር መነሻው ዘመነ ፍጥረት ነው፡፡ ዘመን ራሱ የተፈጠረው ለፍጡር ነው፡፡ ባሕረ ሐሳብ ዘመንን ለመቍጠር መነሻ የሚያደርገው እግዚአብሔር ፍጥረትን መፍጠር የጀመረበትን ዕለት ዕለተ እሑድን አንድ ብሎ ይጀምራል፡፡ ይኽም በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ላይ የተመዘገበውን ታሪክ የተከተለ ሲኾን በዚህ ምዕራፍ እግዚአብሔር ፍጥረታትን በስድስት ቀን እንደፈጠረ በሰባተኛው ቀን ደግሞ እንደዐረፈ ይናገራል፡፡[126] ስለዚኽ በክርስቲያኑ ዓለም ያሉ መምህራን የአንድ ሳምንት የቀን ብዛት ሰባት እንዲኾን የተደረገበት ዋና ምክንያት ይኽ እንደኾነ ያብራራሉ፡፡

መጽሐፈ ሄኖክ የአዳም ሰባተኛ ልጅ የኾነው እና ከቀደምት አበው አንዱ እንደነበረ የሚታወቀው፤ በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደው እና ሞትን እንዳያይ እግዚአብሔር የሰወረው[127] ሄኖክ የተባለ ደግ ሰው የጻፈው ነው[128]፡፡
መጽሐፈ ሄኖክን ስንመለከተው  የኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር እንዲኹም የባሕረ ሐሳብ ፍልስፍናውና መሠረቱ ከሄኖክ መጽሐፍ የተቀዳ መኾኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ባሕረ ሐሳብ የሚያስተምረው ከዚኹ መጽሐፍ ትርጓሜ መነሻነት የተዘጋጀ መኾኑን የሚያሳዩ ብዙ ማስረጃዎች  አሉት፡፡ እንዲኹም የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት ማጣቀሻ አድርገው በዋናነት የሚጠቀሙት መጽሐፈ ሄኖክን ነው፡፡ ይኽንን በጣራ ቅዱስ ኤውስጣጢዎስ ገዳም አገልጋይ የኾኑት አባ ኀይለማርያም የሚባሉ የአቡሻኽር መምህር እና የገዳሙ አበ ምኔት፤ በቃለ መጠይቅ በሚከተለው መልክ አስረድተዋል

‹‹ብዙ ሰዎች የባሕረ ሐሳብ ደራሲ የሚመስሏቸው አቡሻኽር[129] እና ቅዱስ ዲሜጥሮስ እንኳን የተጠቀሙት የሄኖክን ሥራ ነው፡፡ በእርግጥ አቡሻኽርና ቅዱስ ዲሜጥሮስ ለባሕረ ሐሳብ ትምህርት መስፋፋት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል››፡፡[130]

---

[126] ኦሪት ዘፍጥረት  2፥2
[127] ኦሪት ዘፍጥረት 5፥24
[128] ዓለም ከተፈጠረ በ1486 ዘመን እንደተጻፈ መጻሕፍተ ሰሎሞን ወሲራክ ፤ ገፅ 9 ይገልጻል፡፡ ይሁ ቍ.14-15
[129] ENCYCLOPAEDIA Aethiopica,  volume 1, page 56
[130]  ጌታቸው ኃይሌ፡ 1993 ዓ.ም. ፣ገጽ 20

ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ዲሜጥሮስ በ3ኛው መ/ክ/ዘ የነበረ የእስክንድርያ መንበር ሊቀ ጳጳሳት ሲኾን በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት በየዓመቱ አጽዋማትና በዓላት የሚውሉበትን ዕለት[131]፣ እንዲኹም እነዚኹ ዕለታት በየጊዜው በምን ዓይነት መንገድ እንደሚገኙ የቀመሩን ሥርዓትም አዘጋጅቷል፡፡ ቅዱስ ዲሜጥሮስ በዓላትንና አጽዋማትን ሲያወጣ በጸሎትና በሱባኤ ተወስኖ እንደኾነ ይታመናል፡፡[132] እንዲኹም አቡሻኽር ደግሞ በ12ኛው/13ኛው መ/ክ/ዘ የነበረ የእስክድርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዲያቆን ነው፡፡[133] አቡሻኽር ለትምህርቱ መዳበር ላደረገው አስተዋጽኦ ከባሕረ ሐሳብ ትምህርት ክፍሎች መካከል የአንዱን መጠሪያ በስሙ አቡሻኽር ብለው ሰይመውታል፡፡[134] አንዳንድ ጊዜ ባሕረ ሐሳብ የሚለውን አቡሻኽር በማለት የሚጠሩም አሉ፡፡ ስለዚኽ ቅዱስ ዲሜጥሮስና አቡሻኽር የነበረውን ዘመን መቍጠሪያ ተጠቅመው አበለጸጉት ወይም ለአገልግሎት እንዲመች አድርገው አስተካከሉት እንጂ አዲስ ትምህርት አላዘጋጁም፡፡ ይኽም ደግሞ የባሕረ ሐሳብ ትምህርት መነሻ መጽሐፈ ሄኖክ እንደ ኾነ እንረዳለን፡፡

በዋናነት የሚጠቀሱ የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ፣ ኤጲፋኖስ፣ አቡሻኽር፣ ቅዱስ ዲሜጥሮስ፣ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ ወዘተ. ዘመን ለመቍጠር አጠቃላይ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ያለውን የክርስቶስን ልደት መነሻ አድርገው ለኹለት ይከፍሉታል፡፡ መጀመሪያው ከክርስቶስ ልደት በፊት ያለውን ዘመን ዓመተ ፍዳ (የኩነኔ ዘመን) በማለት ይጠሩታል፡፡ የዘመኑ ርዝማኔ (ብዛት) 5500 ዓመት ያህል ነው፡፡[135] ኹለተኛውና ከጌታ ልደት በኋላ ያለው ደግሞ ዓመተ ምሕረት ብለው ይጠሩታል፡፡[136] ለምሳሌ፡ አኹን ያለንበት ዓመት ጌታችን ከተወለደ 2012 ዓመት ኾኖታል፡፡ ዓለም ከተፈጠረ ደግሞ 7512 ዓመት ኾኗል ማለት ነው፡፡ ይኽ ቁጥር የተለያዩ ዑደታዊ ስሌቶችን ለማውጣት በየፈርጁ ጥቅም ላይ እንደሚውል ወደፊት እንመለከታለን፡፡

131 የኔታ አባ ኃ/ማርያም በደቡብ ጉንደር ሀገረ ስብከት የሚገኘው የጣራ ቅዱስ ኤውስጣጢዎስ ገዳም አበ እምኔት እና ለደቀመዛሙርታቸው በነሐሴ ወር ፤ 2008 ዓ.ም. ጥናቱን ለማጥናት የተደረገ የድምጽ ወምስል ቃለ መጠይቅ

132 መ/ር አባ ገ/ሥላሴ ወ/ሚካኤል፡ 2005 ዓ.ም፣ ገጽ 9

133 ጌታቸው ኃይሌ፡ 1993 ዓ.ም. ፣ ገጽ 20

134 ዝኒ ከማሁ

135 መጽሐፈ ቀሌምንጦስ ዋቢ አድረገው "በሐምስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ ወእድሕከ ውስተ መርሕብከ ወእከውን ሕፃነ በእንቲኣከ በመስቀልየ ወበሞትየ" ይላሉ፡፡ መሪጌታ ዘነበ ሐየሎም፡ 2009 ዓ.ም. ኹሉም የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት የሚጠቀሙት መነሻ ቍጥር ነው፡፡

136 አለቃ ያሬድ ፈንታ፤ 2004 ዓ.ም

# የባሕረ ሐሳብ ትምህርት ለዘመን አቈጣጠር፣ ለከዋክብት እና ለአየር ትንበያ

## የተለያዩ ክስተቶች ዑደት ከሰው ልጅ ሕይወት ጋር ያለው ግንኙነት

ዋናው ለዘመን አቈጣጠር አጀማመር ምክንያት የኾነው የሰው ልጆች ከታሪክና ከተፈጥሮ ክስተቶች ጋር ትስስር ያለውን በሕይወታቸው ትናንትና ወይም ዛሬ የተከናወኑ እንዲኹም ለነገ ተግባር አስቀድሞ ለመዘጋጀት ይቻል ዘንድ ታስቦ የተቀመረ ስሌት ነው፡፡

ዘመን መጀመሪያም ኾነ መጨረሻ ባይኖረውም[137] በዓለማችን ውስጥ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ተመልሰው የሚመጡና የተወሰነ ጊዜ ቆይተው የሚኼዱ ነገሮች ወይም የተፈጥሮ ክስተቶች[138] አሉ፡፡ ዘመንን መለካት ወይም መቍጠር ያስፈለገበት ዋናው ምክንያትም የተፈጥሮ ክስተቶች መመላለስ ነው፡፡ እነዚኽ የተፈጥሮ ክስተቶች ምልልሳቸው ከሰው ልጅ ቁጥጥር ውጭ ስለኾነ ተመልሰው የሚመጡበትን ጊዜ ማወቅና ሲመጡ እየጠበቁ መታዘዝ ወይም ከተቻለ ከተጽዕኖዎቻቸው ለማምለጥ ዘዴ መፈለግ የግድ ይኾናል፡፡[139] የሰው ልጅ ሕይወቱን የሚመራው በአብዛኛው እነዚሁ የተፈጥሮ ክስተቶች በሚያዝዙት መሠረት ነው ፤ ከተፈጥሮ ተፅዕኖ ውጭ የኾነ ሙሉ ነፃነት የለንም፡፡[140] እነዚኽ በዓለማችን ውስጥ ያሉት ተመላላሽ ክስተቶች በሰው ሕይወት ውስጥ የራሳቸውን ተፅዕኖ ስለሚያሳድሩ፤ ሰው በሰላምና በጤና ለመኖር ተመላላሽ ክስተቶችን ለይቶ ማወቅ አለበት፡፡ የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት የዘመን መለዋወጥ ከከዋክብት፣ ከጨረቃና ከፀሐይ ዑደት ጋር የተያያዘ መኾኑን ይናገራሉ፡፡[141] ስለዚኽ የዘመን መለዋወጥ በእነዚኽ ፍጥረታት ተፅዕኖ ውስጥ

---

[137] ኹለት ዓይነት ጊዜ አለ፡፡ “መጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድር ፈጠረ፡፡” ዘፍ 1፥1 ይላል በዚኽ አገላለጽ “መጀመሪያ” የሚለው ቃል የሚታወቅና የማይታወቅ ነው፡፡ የሚታወቀው በእግዚአብሔር ነው፡፡ ለሰዎች ወይም ለፍጥረታት ደግሞ የፈጣሪ ጊዜ መጀመሪያውና መጨረሻው አይታወቅም፡፡

[138] የተፈጥሮ ክስተት የሚባሉ እንደ ድርቅ፣ አውሎ ነፋስ፣ ከመጠን በላይ በኾነ ዝናብ የሚከሰቱ ክስተቶች ወዘተ. ለማለት ነው፡፡በጌታቸው ኃይሌ አገለላለጽ ግን ክረምትና በጋ፤ ቀንና ሌሊት ፤ ወዘተ. እንደ ክስተት ተገልጸዋል፡፡

[139] ጌታቸው ኃይሌ ፣ 1993 ዓ.ም፡፡


[140] ዝኒ ከማሁ

[141] ዝኒ ከማሁ

ከወደቀው የሰው ልጅ ሕይወት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ይኖራቸዋል ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ሰው በዘመን ውስጥ የሚያልፍ (ከዘመን ውጭ መኾን የማይችል) ስለኾነ ነው፡፡

# አዕዋዳት

ተመሳሳሽ ክስተቶች (የተፈጥሮ ምልክቶች) ተመላልሰው ለመከሰት የሚወስድባቸው ዘመን ወይም ጊዜ ዐውድ ይባላል፡፡ ዑደት ማለት ዙሪያ ማለት ሲኾን ዐውዶች (በግዕዙ አዕዋድ) ይመላለሳሉ፤ ዞረው ይገጥማሉ ማለት ነው፡፡[142]




ዘመን የሚቆጠረው በክስተቶች ዑደት ላይ ተመሥርቶ ነው፡፡ በመጽሐፈ ሄኖክ መሠረት ሦስቱ አዕዋዳት ማለትም ዐውደ ዕለት፣ ዐውደ ወርኅና ዐውደ ዓመት በተጨማሪም ዐውደ ጳጉሜን በግልጽ በስም ተጠቅሰው የተጻፉ መሠረታዊ አዕዋዳት ናቸው፡፡ የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት በእነዚኽ መሠረታውያን አዕዋዳት ተነሥተው ሌሎችን የተለያዩ የተፈጥሮ ክስተቶችን የሚያመለክቱ አዕዋዳትን አዘጋጅተዋል፡፡ አዕዋዳትም፡-

## ሀ. ዐውደ ዕለት

በቀንና በማታ የሚከፈልና በየ24 ሰዓታት የሚመላለስ ዐውድ ነው፡፡ የአንዱ ዕለት ርዝማኔ በሰዓት ይለካል፡፡ በአኹኑ ጊዜ የአንድ ዕለት ርዝማኔ 24 ሰዓታት እንደኾነ

[142] ዝኒ ከማሁ

በኹሉም የዘርፉ ሊቃውንት ዘንድ ስምምነት አለ። መጽሐፈ ሄኖክ ግን አንድ ዕለት 18 ክፍሎች እንዳሉት ይናገራል።[143]

በመጸሐፈ ሄኖክ አገላለጽ መሠረት የአንድ ቀን ርዝማኔ 18 ክፍል ነው። አኹን በዓለም አቀፍ ስምምነት መሠረት የአንድ ዕለት ርዝማኔ 24 ሰዓታት ወይም 1440 ደቂቃ ነው። ይኽን ዓለም የተስማማበት የአንድ ዕለት ደቂቃ በሄኖክ አቈጣጥር ብንቀይረው በአንድ ሰዓት (ክፍለ ዕለት) 80 ደቂቃ ነበር ማለት ነው።

## ለ. ዐውደ ወርኅ

ጨረቃ በግዕዙ ወርኅ ሲኾን በአማርኛው አጠራር አጥሮ ወር እንደተባለ ጌታቸው ኃይሌ ያስረዳሉ ዐውደ ወርኅ በርዝማኔው ከዕለት ቀጥሎ ሲመላለስ በትክክል የሚታይ የተፈጥሮ ክስተት የጨረቃ ዑደት ነው፡ ጨረቃ በ29 ወይም በ30 ቀናት ውስጥ ወደነበረችበት ትመለሳለች። ስለዚኽ ዐውደ ወርኅ በየ30 ዕለታት የሚመላለስ ዑደት ነው ማለት ነው።

በመጽሐፈ ሄኖክ ምዕራፍ 22 አገላለጽ ጨረቃ የ29 እና የ30 ዕለት ርዝማኔ እያፈራረቀች እንደምትታይ እንዲኹም ሙሉ ብርሃን የምትሰጠው በወሩ አጋማሽ ማለትም 14/15ኛው ቀን እንደኾነ ያስገነዝባል።

## ሐ. ዐውደ ዓመት

የቀንና የሌሊቱ ርዝማኔ፣ የዝናብና የፀሐይ ወቅቶች መፈራረቅ፣ በአጠቃላይ በየወራቱ የሚለያዩ ነገሮች ተመልሰው እንደገና የሚመጡበት ዑደት ዐውደ ዓመት ተብሎ ይጠራል። በመኾኑም የአንድ ዐውደ ዓመት ርዝመት በፀሐይ 365 ዕለት በጨረቃ ደግሞ 354 ዕለት እንደየአቈጣጠሩም የፀሐይ ዓመት ወይም የጨረቃ ዓመት እየተባለ ይጠራል።

## መ. ዐውደ ጳጉሜን (ወንጌላዊ)

የአንድ ዐውደ ጳጉሜን ርዝማኔ አራት ዓመታት ነው። ይኽም በግዕዙ ሠግር (leap year) ይባላል። በተጨማሪም በፀሐይ አቈጣጠር በእየዓመቱ የሚተርፉ(የማይቆጠሩ) ስድስት ካልዒቶች በ600 ዓመት ተሰብስበው ጳጉሜን ሰባት ቀናት ትኾናለች።[144]

---

[143] መጽሐፈ ሄኖክ ፤ ምዕራፍ 21

በመጽሐፈ ሄኖክ ምዕራፍ 28 አገላለጽ ጳጉሜን ለብቻ መቈጥር እንዳለባት ማስጠንቀቂያ አዘል መልእክት "ጳጉሜን ከዋክብት የለም ብለው ይበድላሉ" ይላል፡፡ በእዚኽ ምዕራፍ የጳጉሜን ዕለት ብዛት አራት ነው ይላል ምክንያቱን በምዕራፍ 21 ላይ የዓመት ዕለታት ብዛት 364 ስላለ እንደኾነ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት ሽርፍራፊ ጊዜያትን በመሰብሰብ የጳጉሜን ወር ስድስት እንዲኹም በዘመናት ኺደት ሰባት የሚያደርጉበትን ስሌት በተገቢው ኹኔታ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

## ሠ. ዐውደ አበቅቴ

አበቅቴ የግሪክ ቃል ሲኾን በእንግሊዝኛው ኤፓክት (epact) እየተባለ ይጠራል፡፡[145] ዐውደ አበቅቴ በየ19 ዓመታት የሚደጋገም ዑደት ነው፡፡ አበቅቴ መስከረም አንድ ቀን ዐውደ ዓመት ሲጀመር የጨረቃ ዓመታዊ ዕድሜ ማለት ነው፡፡[146] ይኽ በየ19 ዓመቱ አንድ ጊዜ የሚደረገው የፀሐይና የጨረቃ ‹‹ተራክቦ›› /መገናኛ ፣አብረው ጉዞአቸውን የሚጀምሩበት/ ዐውደ አበቅቴ ይባላል፡፡ ይኽ ዐውድ በአንድ ዓመት መቍጠሪያ በኾኑት በፀሐይና በጨረቃ የዓመት ጉዞ ልዩነት መሠረት የተዘጋጀ ነው፡፡ ይኽም ማለት ሄኖክ አንድ ዓመት 364 ቀን (ሊቃውንቱ ከላይ እንዳየነው አንዷን ዕለት ጨምረው 365 ቀን እና በጨረቃ 354 ቀን መካከል የሚፈጠር የ11 ዕለት ልዩነት የሚፈጠር ዐውድ ነው፡፡ በዚኽ መሠረት በ19 ዓመታቸው ፀሐይና በጨረቃ በአንድ ላይ ጉዞ የሚጀምሩበት ማለት ነው፡፡

## ረ. ዐውደ ማኅተም

የዐውደ ማኅተም ርዝማኔ 76 ዓመታት ነው፡፡ የ19 እና የ4 ትንሹ የጋራ ብዜታቸው (4 x 19) 76 ስለኾነ ዐውደ አበቅቴና ዐውደ ጳጉሜን ዑደታቸውን በአንድ ቀን እኩል የሚጀምሩት በየ76 ዓመቱ ነው፡፡ የመጨረሻው ወንጌላዊ (ዮሐንስ) እና 18 አበቅቴ ይገናኙበታል፡፡[147] ይኽ ዐውድ በ19 ዓመታት የሚፈጠሩ የፀሐይና የጨረቃ ልዩነቶች እና በአራት ዓመት አንድ ጊዜ የሚመጡ ክስተቶች የሚገናኙበት ነው፡፡

---

144 ዝኒ ከማሁ
145 ዝኒ ከማሁ
146 ዝኒ ከማሁ
147 አለቃ ያሬድ ፈንታ፤ 2004 ዓ.ም.

## ሰ. ዐውደ ፀሐይ

የዐውደ ፀሐይ ርዝማኔ 28 ዓመታት ነው፡፡ የዐውደ ዕለት እና ዐውደ ጳጉሜን ዑደቶች የሚገናኙበት ዐውድ ነው፡፡ የ7 እና የ4 ትንሹ የጋራ ብዜታቸው (4 x 7) 28 ስለኾነ የዐውደ ፀሐይ ርዝማኔ 28ኛ ዓመታት ነው፡፡ ለዚኽ ዐውድ መነሻ ፀሐይና ጨረቃ የተፈጠሩት ረቡዕ ስለኾነ፤ ይኽ ዕለት (ዕለተ ረቡዕ) ጥንተ ዮን (ኦን) ይባላል፡፡ ይኽ ዐውድ ኹለቱን መሠረታዊ አዕዋዳት ማለትም ዐውደ ዕለትና ዐውደ ጳጉሜን የሚያገናኝ ነው፡፡

## ሸ. ዐውደ ቀመር

ይኽ ዐውድ በሊቃውንቱ ዐቢይ ቀመር እየተባለ የሚጠራ ሲኾን በ532 ዓመት አንድ ጊዜ የሚፈጸም ዐውድ ነው፡፡[148] ዐውደ ዕለት (በየ7 ዕለቱ የሚመላለስ)፣ ዐውደ ጳጉሜን (በየ4 ዓመታቱ የሚመላለስ) እና ዐውደ አበቅቴ (በየ19 ዓመታቱ የሚመላለስ) ዞረው የሚገናኙበት በየ532 ዓመታት አንድ ጊዜ ነው፡፡ ይኽ ዑደት ዐውደ ቀመር ይባላል፡፡ በዚኽ ዐውድ በሄኖክ የተጠቀሱት አዕዋዳት ኹሉ የሚፈጸሙበት ነው፡፡

ከዚኽ በተጨማሪ ቀመረ ዐረብ የሚባልና ርዝመቱም 228 ዓመታት የኾነ ዑደት አለ፡፡ ይኽም የጨረቃ ዓመተ ዓለም የሚታወቅበት ስሌት ነው፡፡[149]

# ባሕረ ሐሳብ በኢትዮጵያ የነበረው አገልግሎት

የባሕረ ሐሳብ ትምህርት በሀገራችን በተለይ ለሦስት ዐበይት ዓላማዎች ጥቅም ላይ ሲውል እንደነበር እንገነዘባለን፡፡ ይኸውም ለመንፈሳዊ አገልግሎት፤ የተለያዩ ጉዳዮችን ክስተት ለመተንበይ እና የታሪክ መዛግብትን ለማረጋገጥ ነው፡፡

### *ሀ. ለመንፈሳዊ አገልግሎት*

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ መስከረም አንድ ቀን የዓመቱ ተንቀሳቃሽ በዓላት እንደ ትንሣኤ፣ ደብረ ዘይት፣ ሆሣዕና፣ ስቅለት፣ ዕርገትና ጰራቅሊጦስ የመሳሰሉት ቀናት፣ እንዲኹም የመነሻ ቀናቸው ተወስኖ የማይታወቁ አጽዋማት እንደ ዐቢይ ጾም፣ ጾመ ሐዋርያትና ጾመ ድኅነት የመሳሰሉት

148 ዝኒ ከማሁ

149 *አለቃ ያሬድ ፈንታ*፤ 2004 ዓ.ም

ቀላል በኾነ መንገድ በማውጣት እና በዚኹ አያይዛ የማይንቀሳቀሱ ወይም ዓመቱ ቢቀያየርም ቋሚ የኾኑትን በዓላትና አጽዋማት ለይታ ለምእመኗ ታሳውቃለች፡፡

የሚዘዋወሩ በዓላትና አጽዋማት የሚገኙት (በዓላቱ የሚውሉበትን ፤ አጽዋማቱ የሚገቡበት ቀን የሚታወቀው) አራት ነገሮች በመደመር ነው፡፡ እነርሱም (1) መጥቅዕ ፣ (2) መጥቅዕ የሚውልበት ዕለት ተውሳክ ፣ (3) የበዓላትና የአጽዋማት ተውሳክ እና (4) የነነዌ መባጃ ሐመር (የነነዌ ጾም የሚገባበት ወርኃዊ ቀን) ናቸው፡፡ [150] በየቀኑ የአሥርቆቱን ሥርዓት ታደርሳለች፡፡ አሥርቆት ማለት የሌሊት መባቻ በጨረቃ ፤ የመዓልቱን መባቻ በፀሐይ ቆጥሮ መናገር ነው፡፡[151] ሌሊቱን ለማውጣት አበቅቴና ዕለቱን (በፀሐይ) ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ በመኾኑም የሚከተለው ቀመር የእያንዳንዱን ዕለት ሌሊት ለማግኘት ያገለግላል፡፡

ሌሊት = አበቅቴ + ዕለት + የወሩ ሕፀፅ

ለምሳሌ፦ የ2012 ዓ.ም. የመስከረም 1 (አንድ) ቀንን የአሥርቆት ሥርዓት እንመልከት፡፡

ዓመቱ፡ በፀሐይ 2012 ዓመት፤ በጨረቃ 2070 ዓመት ከ11 ወር፤ ከ 16 ቀን ነው፡፡

- የሌሊት መባቻ በ 24 ፣ የጨረቃ መባቻ በ 28 ፣ እንዲኹም የመዓልቱ መባቻ በ 1 እንደሚኾን በማስላት እና ቀኖቹን እንዲኽ ለይቶ በማውጣት ለእየራሱ ጸሎት ይደርሳል፡፡

## ለ. ለትንበያ አገልግሎት

የዘመን መለዋወጥ የፀሐይ፣ የጨረቃ፣ የከዋክብትን ዑደት እና የነፋሳትን ኹኔታ ተከትለው የሚመጡ የወቅቶች መለዋወጥ እንዲኹም እነዚኽን ምክንያት በማድረግ የሚመጡ የተለያዩ ክስተቶችን በማየት የሰዎች የኑሮ ኹኔታ ላይ ወደፊት ሊኾኑ የሚችሉ ነገሮችን ለመተንበይ የባሕረ ሐሳብን ዘዴዎች ይጠቀሙበት ነበር፡፡ እንዲኹም አንዳንድ ሊቃውንት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም የሚመጣበት ቀን መቼ ሊኾን እንደሚችል የነቢያትን ትንቢት መነሻ በማድረግ ይተነብያሉ፡፡ በዚኽ ትንቢት መሠረት ጌታችን 8000 ዓመት ሳይሞላ ወይም ትንሽ ሲያጎድል

[150] መርሐ ዕውር

[151] አለቃ ያሬድ ፈንታ ፤ 2004 ዓ.ም

እንደሚመጣ የሚናገሩ አሉ።[152] በዚኽም የተነሣ ይመስላል ብዙ የባሕረ ሐሳብ መምህራን 7980 ዓመት ላይ ሲደርሱ ዘመኑን መቍጠር ያቆማሉ።

### *ሐ. የታሪክ ክስተቶችን፣ መዛግብትን ትክክለኛነት ለማወቅ እና ለማረጋገጥ*

የኢትዮጵያ ሊቃውንት በባሕረ ሐሳብ ትምህርትና የአቈጣጠር ስሌታቸው በመታገዝ የታሪክ ድርሳናትን ማረጋገጥ እንደሚችሉ ያስረዳሉ።

ለምሳሌ፦ ክርስቶስ የተወለደው ታኅሣሥ 29 ቀን ፣ ማክሰኞ ዕለት መኾኑን እንዲኽ ያረጋግጣሉ ፡ ይኽንን ለማስላት ፀሐይና ጨረቃ ዑደታቸውን በእኩል ጊዜ ከጀመሩ ምን ያኽል ዓመት እንደኾናቸው መቍጠሪያ የኾነውን አበቅቴ የሚባለውን ማግኘት አስፈላጊ ነው። ስለዚኽም የፀሐይን አበቅቴ ለማወቅ ሲፈልጉ ዘመኑን በዓመተ ዓለም (5500 + ከክርስቶስ ልደት ወዲኽ ያለውን ዓመት) ይወስዱና ያለንበት ዘመን ገና ስላላለቀ አንድ ቍጥር ያነሡለታል (አንድ ለዘመን ተው የሚለውን ዐዋጅ በማስታዉስ)[153]። [154]የተረፈውን ከአራት ቦታ ከፍለው አንዱን ክፍል (ሩቡን) በዋናው ላይ ይደምሩበታል። ሩቡን ለማውጣት ከአራት ቦታ ሲከፈል የአራቱ ግማሽ ኹለት ወይም አራት ሩብ ከተረፈ አብረው ይደምሩታል፤ ያለዚያ ደግሞ ይጥሉታል። ጠቅላላውን ድምር በሰባት ገድፈው (ለሰባት አካፍለው)፤ የሚተርፈውን የዚያ ዓመት የፀሐይ አበቅቴ እንደሚኾን ደንግገው አስቀምጠዋል። የፀሐይ አበቅቴ የሳምንቱን ዕለት ማወቅያ ነው። ስለዚኽ ይኽን አሠራር ተከትለው የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ልደት ማክሰኞ ዕለት እንደዋለ አረጋግጠዋል።

## የዘመን አቆጣጠር

የተለያዩ ዐውዶችን በመጠቀም አጽዋማትና በዓላትን ለማውጣት፣ ዘመኑ በፀሐይና በጨረቃ ለየብቻ ስንት እንደኾነ አስልቶ ማወቅ ያስፈልጋል። የቍጥር ስሌቱን ለማስተማር ብዙ ዓመታትን በዐውድ ማካፈል ስለሚያስፈልግ መጀመሪያ ከመጀመሪያው ዐውድ ይነሡና ዐውዱ በጨመረ ቍጥር ከእያንዳንዱ ዐውድ

[152] መጽሐፈ ዞሲማስ፣ ጌታቸው ኃይሌ፡ 1993 ዓ.ም.፣መርጌታ ዘነበ ሐየሎም፤

[153] ጌታቸው ኃይሌ፡ 1993 ዓ.ም.

[154] ለዘመን አንድ ተው የሚልበት ምክንያት ስለተጀመረ ይቈጠራል ስላልተፈጸመ ይቀነሳል፤ በዚኽ ምሳሌ ለማስረዳት የ5500 ዓመትን ታህሣሥ 29 ለማወቅ አንድ ይቀነሳል፤ ምክያቱም ለመደመር ገና ወደፊት ያሉ 8 ወራቶች አሉ የማታወቁ፤ እንዲኹም ለመቀነስ አራት ወሮች አልፈዋል ስለዚኽ ለመቍጠርም ለመተውም ስለሚያስቸግር መቀነሱ የተሻለ ነው። በሒሳብ(mathematics) ትምህርት ሙሉ ቍጥር የሚጀምርው ከዜሮ ነው። በባሕረ ሐሳብ መምህራንም ዘንድ ሙሉ ቍጥር ለመጀምር ይመስላል አንድ በመቀነስ ይጥራሉ።

የሚተርፈውን ቍጥር ልዩነቱን በመያዝ ቀሪውን ብቻ በመቍጠር ምን ያኽል እንደኾነ በቃላቸው ያሰላሉ። ዘዴው[155] አንድ የተሰጠ ቍጥርን በቀሪ ማካፈል (modular arithmetic and algebra) ሲኾን ቀሪ (remainder) ለባሕረ ሐሳብ እጅግ አስፈላጊ ነው። ሄኖክ በዋናነት ተካፋይ ቍጥሮችን የሚጠቀም ሲኾን በቀሪ የሚካፈሉትን የመጽሐፈ ሄኖክ የተረጎሙ ሊቃውንት አካተውታል። ለምሳሌ አንድ ዓመት 364 ቀን ነው የሚለው ሲያብራሩ 5ኛይቱን ቀን ከሱባኤ አትገባም ብሎ ተዋት ይላል።[156]

ዘመንን ለመቍጠር በሄኖክ አገላለጽ የሰማይ ምሥጢር ብሎ በምዕራፍ 21 እስከ 28 የገለጻቸውን በዋናነት የፀሐይንና የጨረቃን ዑደት ማወቅ ያስፈልጋል። ይኽም የኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጥር መነሻው የሮም ከተማ መቆርቆርን መሠረት ካደረገው ከጎርጎርዮሳውያን አቈጣጠር ልዩ እንዲኾን ያደርገዋል።[157] ኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር ከምዕራባያውን እንዲለይ የሚያደርገው መነሻው የሥነ መለኮት ትምህርት መኾኑ እና ማገናዘቢያውም (ማመሳከሪያውም) ሥነ ፍጥረት መኾኑ ነው።[158]

## ዑደተ ፀሐይ

የአንድ ዓመት ርዝመት በፀሐይ 365 ዕለት ከ15 ኬክሮስ ከ6 ካልዒት ነው። የብርሃን መጠኗ ከጨረቃና ከከዋክብት ይበልጣል። የባሕረ ሐሳብ መምህራን ፀሐይ የተፈጠረችው እሑድ ከተፈጠረው ብርሃን ነው ይላሉ።[159]

የፀሐይ የጕዞ መስመር ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ሲኾን በምሥራቅ ስድስት መስኮቶች (መውጫ) ፤ በምዕራብም እንዲኹ ስድስት መስኮቶች (መግቢያ) አሏት። ፀሐይ በምዕራብ ከገባች በኂላ በበነጋው በሰሜን በኩል ዞራ በምሥራቅ ትወጣለች። ስለዚኽ ዑደቷ የሰዓት ተቃራኒ (counter clockwise) ነው ማለት ነው።

ይኽም ማለት ፀሐይ ከሰሜን ወደ ደቡብ ወይም ከስድስተኛው ደጃፍ ወደ አንደኛው ደጃፍ ስትመለስ ቀኑ ያጥራል። ምክንያቱም ፀሐይ ወደ ሰሜን ስትዞር ከምድር ዋልታ በአጭር ርቀት ስለምትገኝ የወሩ ርዝማኔ በሽርፍራፊ ሰዓት ያንሳል። የእየወሩ

---

155 ባሕረ ሐሳብ ትምህርት የሚሰጥበት የተለመደው የማስተማሪያ ዘዴ በቃል ወይም በንባብ የሚሰጥ ሲኾን በዚኽ የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች እየጻፉ ሳይኾን በመስማት ብቻ የሚከናወን ነው።

156 የመጽሐፈ ሄኖክ አድምታ፤ ምዕራፍ 21 ፤ በዚኽ አገላለጽ ሱባኤ ማለት ሰባት ለማለት ወይም በሰባት ስለማይካፈል።

157 ኅሩይ ሰሜ፡ ትክክለኛው የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር፡ 2000 ዓ.ም. ገጽ 77

158 ዝኒ ከማሁ

159 መጽሐፈ አክሲማሮስ ዘረቡዕ፣

የዕለት ሰዓትም በፀሐይ አቀማመጥ ምክንያት አንዱ ዕለት ከሌላው ዕለት እንዲበላለጥ ያደርገዋል፡፡[160] እንዲኹም ፀሐይ ከደቡብ ወደ ሰሜን ወይም ከአንደኛው ደጃፍ ወደ ስድስተኛው ደጃፍ ስትሄድ ቀኑ ይረዝማል፡፡

በሄኖክ የአንድ ዕለት ርዝማኔ 18 ክፍል እንደኾነ ከላይ ተገልጿል፡፡ ስለዚኽ የመዓልትና የሌሊት ሰዓት ወይም ክፍል በየወሩ ከሚወጡ ከዋክብት አንጻር ያላቸውን ንፅፅር በሚቀጥለው ሠንጠረዥ መመልከት እንችላለን፡፡

ሠንጠረዥ 1፡ በየወሩ ከሚወጡ ከዋክብት አንጻር ያላቸውን ግንኙነት ከመዓልት አንጻር

| ተ.ቁ. | ወር | አንድ ዕለት 24 ሰዓት በማድረግና አሁን በዓለም አቀፍ አገልግሎት ላይ ያለው | | በሄኖክ አገላለጽ መሠረት አንድ ዕለት 18 ክፍል በማድረግ | | የወሩ ኮከብ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የመዓልቱ ሰዓት | የሌሊቱ ሰዓት | የመዓልቱ ክፍል | የሌሊቱ ክፍል | |
| 1 | *መስከረም* | *12* | *12* | *9* | *9* | *ሰንቡላ* |
| 2 | ጥቅምት | 11 | 13 | 8 | 10 | ሚዛን |
| 3 | ኅዳር | 10 | 14 | 7 | 11 | አቅራብ |
| 4 | *ታኅሣሥ* | 9 | 15 | 6 | 12 | ቀውስ |
| 5 | ጥር | 10 | 14 | 7 | 11 | ጀደይ |
| 6 | የካቲት | 11 | 13 | 8 | 10 | ደለው |
| 7 | *መጋቢት* | *12* | *12* | *9* | *9* | *ሑት* |
| 8 | **ሚያዚያ** | **13** | **11** | **10** | **8** | **ሐመል** |
| 9 | ግንቦት | 14 | 10 | 11 | 7 | ተውር |
| 10 | ሠኔ | 15 | 9 | 12 | 6 | ጀውዛ |
| 11 | ሐምሌ | 14 | 10 | 11 | 7 | ሸርጣን |
| 12 | ነሐሴ | 13 | 11 | 10 | 8 | አሰድ |

በዚኽ ሠንጠዥ መሠረት የመዓልት(የቀኑ ወይም ብርሃኑ ክፍል) እና የሌሊቱ ክፍል ከወር ወር ይለያያል፡፡ የልዩነቱ መሠረት በመጽሐፈ ሄኖክ ምዕራፍ 21 እንደተገለጸ የፀሐይ መውጫ በእየወሩ መቀያየር ተከትሎ የተፈጠረ ነው፡፡ በዚኽም መሠረት

[160] ዝኒ ከማሁ

ፀሐይ ምድርን እኩል በእኩል የምትከፍላት በዓመት ኹለት ጊዜ ማለትም መዓልቱና ሌሊቱ እኩል በሚኾኑበት በመስከረም እና በመጋቢት ወራት ነው። በትክክል እኩል (Equinox) የሚኾነው መስከረም 25 እና መጋቢት 25 ላይ ነው። [161] ከመስከረምና ከመጋቢት በስተቀር ሌሎች ወሮች የመዓልትና የሌሊት የሰዓት ርዝማኔ እኩል አይደለም።

ሌላው በዚኽ ሠንጠረዥ ለመግለጽ የተሞከረው አሁን የምንገለገልበት አንድ ቀን በ24 ሰዓት ከፍለን ቢኾን የሌሊቱና የመዓልቱ ከወር ወር መለያየት በመጽሐፈ ሄኖክ ላይ በተቀመጠው መሠረት መኾኑን መረዳት ያስፈልጋል። በተጨማሪም በእየወሩ የሚወጡ ከዋክብት በሄኖክ የተገለጸውን መተርጉማን (ተርጓሚዎች) በዚክ መልኩ በስፋት አስቀምጠውታል።
የኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር የዓመት መጀመሪያ ወር መስከረም የኾነበት አንዱ ምክንያት የመዓልትና የሌሊት እኩል መኾኑ ነው።

## የእየዕለቱን ሰዓት መበላለጥ ሊቃውንቱ በምን ሰፍረው ዐወቁት ?

በሄኖክ የአንድ ቀን ርዝማኔ 18 ክፍል እንደኾነ የተገለጸ ቢኖንም የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት ከ18 ክፍል ይልቅ በ24 ሰዓት ከፍለው ለመሥራታቸው ምክንያቱን ማረጋገጥ በዚኽ ጥናት አልተቻለም። የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት በአንድ ቀን ውስጥ ያሉትን ሰዓቶች ያወቁበትን መንገድ እንዲኽ ብለው መዝግበውታል ‹‹አንተ በትክክል የራስህ ጥላ በደረሰበት ላይ ምልክት ታደርጋለህ፤ ሰዓቱን ለማወቅ እግርህን በማፈራረቅ እየሰፈርህ ትቈጥራለህ። ከመዠመሪያው ሰዓተ መዓልት እስከ ሠርክ ዐሠራ ኹለት ሰዓት፤ ከታኅሣሥ ወር እስከ ሠኔ ወር 1 1/2 ጫማ በየወሩ ትቀንሳለህ፣ ዳግመኛም ከሠኔ ወር እሰከ ታኅሣሥ ወር 1 ½ ጫማ በየወሩ ትጨምራለህ።››[162] በማለት በሄኖክ ከወር ወር የሰዓት ልዩነት ለመረዳት ችለዋል።

የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት መጽሐፈ ሄኖክ ምዕራፍ 28 መሠረት በማደረግ የፀሐይን ዑደት በመጠቀም ዓመትን በአራት መድበው በእየሦስት ወሩ የሚወጡ ክዋከብትን ይገልጻሉ። በእያንንዱ በአማካይ ዘጠና አንድ (91) ዕለት፣ ከዐሥራ ስምንት (18) ኬክሮስ፣ ከአርባ አምስት (45) ካልዒት የያዙ ወቅቶች ይገኛሉ[163]። እነርሱም

[161] ጌታቸው ኃይሌ፡ 1993 ዓ.ም
[162] አለቃ ያሬድ ፈንታ፤ 2004 ዓ.ም
[163] ዝኒ ከማሁ

1. **ጸደይ** (ከመጋቢት 26 እስከ ሠኔ 25 ቀን) ፡ በዚኽ ወቅት የሚገኙ ወሮችና ኮከቦች ሚያዝያ /ሐመል/ ፣ ግንቦት /ተውር/ እና ሠኔ /ጀውዛ/ ናቸው። በጸደይ የሚቆመው የሦስት ከዋክብት አለቃ ምልክኤል ይባላል። ወቅቱ የመሬት ጊዜ ነው።
2. **ክረምት** (ከሠኔ 26 እስከ ምስከረም 25 ቀን) ፡ በዚኽ ወቅት የሚመደቡ ወሮችና ኮከቦቻቸው ሐምሌ/ሸርጣን/ ፣ ነሐሴ/ አሰድ/ እና መስከረም /ሰንቡላ/ ናቸው። በክረምት የሚቆመው የሦስት ከዋክብት አለቃ ሕልመልሜሌክ ይባላል። በመኾኑም ወቅቱ የውኃ ጊዜ ነው።
3. **መፀው** (መስከረም 26 እስከ ታኅሣሥ 25 ቀን) ፡ በዚኽ ወቅት የሚመደቡ ወሮችና ኮከቦቻቸው ጥቅምት /ሚዛን/ ፣ ኅዳር/አቅራብ/ እና ታኅሣሥ/ቀውስ/ ናቸው። በመፀው የሚቆመው የሦስት ከዋክብት አለቃ ምልኤል(ሚላኤል) ይባላል።ወቅቱ የነፋስ ጊዜ ነው።
4. **በጋ** (ከታኅሣሥ 26 እስከ መጋቢት 25 ቀን) ፡ በዚኽ ወቅት የሚመደቡ ወሮችና ኮከቦቻቸው ጥር/ጀደይ/ ፣ የካቲት /ደለው/ እና መጋቢት/ሑት/ ናቸው። በበጋ የሚቆውመ የሦስት ከዋክብት አለቃ ናርኤል ይባላል። ወቅቱ የእሳት ጊዜ ነው።

## ኬክሮስና ክንትሮስ

ኬክሮስ፡- ትርጉሙ የመሬት ትልቅ ክፍል (መሬት ላይ በሐሳብ የተሰመረ ረጅም መስመር) ማለት ሲኾን ከደቡብ እስከ ሰሜን የተዘረጋ ፤ ሌሊቱና መዓልቱ ተለይቶ የሚታወቅበት መክፈያ ነው። ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ያለው የኬክሮስ ብዛት ስድሳ ነው።[164]

ክንትሮስ ፡- ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ የተዘረጋና ምድርን በሐሳብ የሚከፍል መስመር ነው። ክንትሮስ ከኬክሮስ ጋር እንደ ጥብጣብ አልጋ የተሠራ የረጋ ነፋስ ስለኾነ እንደ ምድር ኾኖ ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት ይጓዙበታል።[165] ይኽም ማለት የፀሐይን እና የጨረቃን የጉዞ መስመር ለይቶ ለማወቅ የሚያገለገል መለኪያ ይኾናል ማለት ነው።

[164] ጌታቸው ኃይሌ ፤ 1993 ዓ.ም.
[165] አለቃ ያሬድ ፈንታ ፤ 2004 ዓ.ም.

የኬክሮስ መጠን 16 ዓመት ከ8 ወር ያኽል የሚፈጅ ሲኾን ይኽም እንደሚከተለው ሊከፋፈል ይችላል፡፡[166] 1 ኬክሮስ ፡ 6 ክንትሮስ ፤1 ሰዓት፤ 5 ኬክሮስ (30 ክንትሮስ) ነው፡፡ ስለዚኽ 1 ዕለት፡ 60 ኬክሮስ ፤1 ኬክሮስ፡ 60 ካልዒት[167]፤1 ካልዒት፡ 60 ሣልሲት[48] ፤1 ሣልሲት ፡ 60 ራብዒት[49]፤ 1 ራብዒት፡ 60 ኃምሲት[50] 1 ኃምሲት፡ 60 ሳድሲት[51] ይኾናል ማለት ነው፡፡

## ዑደተ ጨረቃ (ወርኀ)

ጨረቃ በዋናነት ሊሊቱን ለመቍጠር የምታገለግል ናት፡፡[168] በእየዕለቱም የራሷን ቅርፅ ስለምትለውጥ፤ እያንዳንዱ የጨረቃ ቅርፅ ራሱን የሚደግመው በየኻያ ዘጠኝ ወይም በየሠላሳ ቀን ነውና፡፡ ጨረቃ ሙሉ (full moon) በኾነች ጊዜ የብርሃን መጠኗ የፀሐይን አንድ ሰባተኛ (1/7) ያኽል ነው፡፡[169] ጨረቃ የምትወጣው በምሥራቅ ሲኾን የምትገባውም እንደ ፀሐይ በምዕራብ ነው፡፡ ጥንተ ዮን (ጨረቃ ለመጀመሪያ ጊዜ የታየችው) ለጨረቃ ሐሙስ ነው፡፡

ጨረቃ በምትወለድበት/በምትወጣበት ጊዜ ወደ ክቡ የሚገባው ቅርፃ (የማጭድነቱ ቅርፅ) ወደ ምሥራቅ ኾኖ ፀሐይ ስትጠልቅ በአራት ኬክሮስ ርቀት ትወጣለች፡፡ አንድን ሌሊት ሙሉ 60ውን ኬክሮስ የምታበራው መታየት ከጀመረች በ14/15 ኛው ቀን ነው፡፡ ስለዚኽ አማካይ የዕለት መንገዷ 59 ኬክሮስ 3 ካልዒት 40 ሣልሲት 16 ራብዒት 18 ኃምሲት ከ48 ሳድሲት ሲኾን በዚኽ ጉዞዋ ከምዕራብ ሳትደርስ ወይም 56 ካልዒት 19 ሣልሲት 43 ራብዒት 41 ሐምሲት ከ12 ሳድሲት ሲቀራት ፀሐይ 60ውን ኬክሮስ ፈጽማ በምሥራቅ ትታያለች፡፡ እንዲኹም ኻያ ቀን ሲኾናት (በኻያኛው ቀን) በቀን (በመዓልት) እና በማታም (በሌሊትም) ትታያለች፡፡ ሄኖክ እንደሚለው በሃያ ቀኗ በሌሊት ሰው መስሎ በቀን ሰማይ መስሎ ይታያል ይላታል፡፡[170]

የዓመቱን አጠቃላይ በዓላት፣ አጽዋማት፣ አሥርቆት ወዘተ ለማውጣት አበቅቴና መጥቅዕ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

---

[166] ዝኒ ከማሁ
[167] ካልዒት ማለት ሁለተኛ ማለት ሲሆን ከኬክሮስ ቀጥሎ የሚሰላበት የጊዜ መለኪያ
[168] ኦሪት ዘፍጥረት 1፡16
[169] መጽሐፈ አክሲማሮስ ዘኤጲፋኖስ
[170] መጽሐፈ ሄኖክ ምዕራፍ 22

## ሀ. አበቅቴ

ጥንተ አበቅቴ[171] የሚባለው በእየዓመቱ በፀሐይና በጨረቃ መካከል የሚፈጠሩ ልዩነቶች ናቸው፡፡ በየዓመቱ አበቅቴው ስለሚለያይ በተያዘው ዓመት አበቅቴ ላይ 11 ቢደመር የሚመጣው ዓመት አበቅቴ ፣ 19 ቢደመር ደግሞ ያለፈው ዓመት አበቅቴ ይገኛል፡፡

## ለ. መጥቅዕ

መጥቅዕ ማለት ጨረቃ በዓመቱ የመጀመሪያው ወር (30 ቀን) የሚሞላበት የዕለት ቍጥር ነው፡፡ መጥቅዕ የቃሉ ትርጉም ደወል ማለት ሲኾን አጽዋማት እና በዓላትን ለማውጣት ይጠቅማል፡፡ የመጥቅዕና የአበቅቴ ድምር ኹልጊዜ ሠላሳ ነው፡፡

እያንዳንዱ ዓመት ላይ በፀሐይም ኾነ በጨረቃ ቈጥሮ በስሌት ለማግኘት በመጀመሪያ ከጌታችን ልደት በፊት ያለውን ጊዜ ዓመተ ፍዳ እና ከጌታችን ልደት ወዲኽ ያለውን ዓመተ ምሕረት (በፀሐይ) በመደመር፤ በቀመረ ዐረብና በንዑስ ቀመር በመቀመር በጨረቃ የዓመቱ ቍጥር ምን ያኽል እንደ ኾነ ማወቅ ይቻላል፡፡

ለምሳሌ፡- የ2012 ዓመት ማለትም ከልደተ ክርስቶስ ጀምሮ እስከ ዛሬ ያለውን 2012 ዓመተ ፀሐይ በጨረቃ ስንት ዓመት እንደኾነ ለማስላት በመጀመሪያ ዓመተ ፀሐይን በቀመረ ዐረብ ፣ በንዑስ ቀመር መቀመር ያስፈልጋል፡፡ ይኸም ማለት፡-

2012 ÷ 228 = 8 ቀመረ ዐረብ ኾኖ፤ 188 ዓመት ይተርፋል፡፡ ትርፉን (ቀሪውን) በንዑስ ቀመር እንቀምረዋለን (እናካፍለዋለን)፡፡

188 ÷ 19 = 13 ንዑስ ቀመር ኾኖ፤ 13 ዓመተ አበቅቴ ይተርፋል፡፡ ከዚኽ በኋላ ከቀመረ ዐረብ የሚገኘውን በ7 ዓመት፤ ከንዑስ ቀመር የሚገኘውን በ7 ወር፤ ለንዑስ ቀመር ስናካፍል ያገኘነውን ዓመተ አበቅቴ ደግሞ በ 11 ዕለት (በጥንተ አበቅቴ) እናባዛለን፡፡

መጨረሻ ካገኘነው ዓመተ አበቅቴ አንድ ዓመት መቀነሱን ልንዘነጋ አይገባም፡፡[172] ይኸም የያዝነው ዓመት ገና ስላልተጠናቀቀ ነው፡፡ እንዲኹም ለጨረቃ ዘመን መሠረት የኾነውን 4 ወር ከ 10 ቀን ፣ ከትራፋተ ዐውድ የተገኘውን 24 ዕለት

[171] ጥንተ አበቅቴ ማለት የመጀመሪያው በፀሐይና በጨረቃ መካከል የተፈጠረው የ11 ዕለታት ልዩነት ማለት ነው፡፡

[172] አዋጅ ነው፡፡

መደመርም ያስፈልጋል፡፡[173] እነዚኽ ዕለታት ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ በየዓመቱ ከሚተርፉት ተሰብስበው የተገኙ ናቸው፡፡

ስለዚኽ 8 ቀመረ ዐረብ × 7 ዓመት = 56 ዓመት

13 ንዑስ ቀመር × 7 ወር = 91 ወር (91 ወር ማለት 7 ዓመት ከ 7 ወር ማለት ነው፡፡)

12(13 - 1) ዓመተ አበቅቴ × 11 ዕለት = 132 ዕለት (132 ዕለት ማለት ደግሞ 4 ወር ከ 12 ቀን ማለት ነው፡፡)

ይኽ ኹሉ በአንድ ላይ ሲደመር 63 ዓመት (56+7) ከ11 ወር (7+4) ከ 12 ዕለት ይኾናል፡፡ ይኽንን የአገኘነውን ዓመት ከዓመተ ፀሐይ አንድ ዓመት ከአነሣንለት በኋላ ቀሪው ላይ እንደምረዋለን፡፡ በመኾኑም

2011(2012 - 1) + 63 ዓመት 11 ወር 12 ዕለት = 2070 ዓመት ከ11 ወር 12 ዕለት ይኾናል፡፡

ይኽም ማለት ክርስቶስ ከተወለደ ጀምሮ (በፀሐይ) መስከረም 1 ቀን 2012 ዓ.ም በዓመተ ጨረቃ ሲሰላ 2070 ዓመት ከ11 ወር ከ12 ዕለት ኾኖታል ማለት ነው፡፡

በአጠቃላይ ዘመንን ለመቁጠር መነሻውን ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ በሐሳበ ዲሜጥሮስ የቀመር መነሻው ዕለት (ጥንተ ቀመር) ማክሰኞ ሲኾን፣ የሐሳበ ቢዘን ጥንተ ቀመር እሑድ እንዲኹም የሐሳበ ጉንዳጉንዲ ዓርብ ናቸው፡፡ ሦስቱም ሐሳቦች መነሻቸውን ለመወሰን እና ልዩነቱን ለመግለጽ የየራሳቸው አመክንዮ ያቀርባሉ፡፡[174]

በአጠቃላይ ባሕረ ሐሳብ በኹለቱ አዕዋዳት ማለትም የፀሐይና ጨረቃ ዑደት በመጠቀም በኹለቱም እንደ አስፈላጊነታቸው የሚቆጥር ልዩ የኾነ የዘመን መቍጠሪያ ኾኖ የሚያገለግል ነው፡፡ ዘመንን ለመቍጠር በዋናነት የዓለምን ዘመን መክፍያ የኾነውን የጌታችንን ልደት ሊቃውንት የክርስቲያን ዘመን መጀመሪያ ብለው ተርተውታል፡፡[175] ይኽም የኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጥር ከሌሎች በተሻለ ነገረ መለኮታዊ ይዘት ያለው እና፤

[173] አለቃ ያሬድ ፈንታ፤ 2004 ዓ.ም. ገጽ 154
[174] ዝኒ ከማሁ
[175] ኀሩይ ሰሜ፡ ትክክለኛው የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር፡ 2000 ዓ.ም. ገጽ 75

# ሥነ ከዋክብት

በመጽሐፈ ሄኖክ ምዕራፍ 24 በስፋት እደተጠቀሰው ከዋክብት በስም እየጠራ የሚቆዩበትን የጊዜ ርዝማኔ ይገልጻል። ከዋክብት ጨረቃ ጋር በሌሊት ያበሩ ዘንድ የተፈጠሩ ናቸው።[176] የብርሃን መጠናቸው ከጨረቃ ያነሰ ነው። ቅርፃቸውም እንደ ፀሐይና ጨረቃ ክበብ ሳይኾን የተለያየ ቅርጽ አላቸው። ለምሳሌ የአይሁድ ኮከብ የሚባለው ባለስድት ጫፍ አለው።

የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት የከዋክብት ብዛት እንደማይታወቅ እና የብርሃን መጠናቸው አንዱ ኮከብ  ከሌላው እንደሚበላለጡ እንዲኹም ብርሃን የሌላቸው ከዋክብት መኖራቸውን ይናገራሉ። "መጽሐፍ አንዱ ኮከብ ከሌላው ኮከብ ይበልጣል"[177] ኹሉም ክዋክብት እኹልና ተመሳሳይ አይደሉም። በእየዕለቱና በእየወሩ የማይወጡ ከዋክብት ማለትም በኾኑ ዘመናት ልዩነት አንድ ጊዜ የሚታዩ ከዋክብት አሉ።[178]

የከዋክብት ትምህርት በባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት ዘንድ የሚሰጥበት ምክንያት ከዋክብት እንደ ፀሐይና ጨረቃ ኹሉ ለዘመን መቍጠሪያነት የሚያገለግሉ ስለኾኑ እና የዘመን መለዋወጥን ተከትለው የሚከሰቱ ክስተቶች ከከዋክብት ጋር ግንኙነት ስላላቸውም ጭምር ነው። ስለዚኽ የከዋብትን ትምህርት በኹለት ከፍለን እንመልከት።

# የከዋክብት ዓይነታቸውና ጠቀሜታቸው

የባሕረ ሐሳብ ትምህርት ዘመንን እንደ ፀሐይና ጨረቃ ኹሉ በከዋክብት ይቈጥራሉ። በከዋክብት አንድ ዓመት ሦስት መቶ ስድሳ አራት ቀን (364) ነው።

የከዋክብትን ከወጡበት ጊዜ አንጻር ለኹለት ከፍለን ማየት እንችላለን ፤ አንዱ ሄኖክ በመጽሐፉ በእየሦስት ወሩ (ስማቸው ዝቅ ብሎ ተጽፏል) ፣ በእየወሩ ፣ በእየዓሥራ ሦስት ቀንና በእየዕለቱ የሚወጡ ከዋክብት በማለት የለያቸው ሲኾኑ እነዚኽንም ከዋክብት ከላይ በሠንጠረዥ 1 እንደተገለጸው በስማቸው ተጠርተዋል።[179] ኹለተኛው የከዋክብት ዓይነቶች ቋሚ መውጫ ዕለት የሌላቸው በተወሰነ የጊዜ ልዩነት የሚወጡ

[176] ኦሪት ዘፍጥረት 1፥16
[177] 1ኛ ቆሮ 15፥ 41
[178] አለቃ ያሬድ፤ 2004 ዓ.ም.
[179] ዝኒ ከማሁ

ናቸው። ለምሳሌ አቅራብ ተብሎ የሚጠራው ኮከብ በስድስት መቶ አንድ ጊዜ ይወጣል።[180]

## የመውጫ ዕለታቸው የሚታወቁ ከዋክብት

ሄኖክ ስለከዋክብት በጻፈበት ምዕራፍ በእየወሩና በእየዕለቱ ለሚታዩ/ ለሚወጡ ከዋክብት ስም ሰጥቷቸዋል። በእርግጥ የከዋክብት ብዛት አይታወቅም ነገር ግን ሄኖክ በእየ ሦስት ወርና በእየዐሥራ ሦስት ቀን የሚወጡ ከዋክብትን ብቻ በስም እየጠራ ዑደታቸውና ሥርዓታቸው እንዴት እንደኾነ በስፋት ጽፎታል። ይኽንን ተከትሎ የባሐረ ሐሳብ ሊቃውንት ስለ ከዋክብት በሚከተለው መልኩ ያስተምራሉ።

የከዋክብት አሰፋፈር/ አቀማመጥ በጨረቃ ዙሪያ ሲኾን የሚወጡበት ጊዜና የሚቆዩበት የጊዜ ርዝማኔ አራት ከዋክብት በእየ ዘጠና አንድ ቀን የሚወጡ /ዘጠና አንድ ቀን የሚያበሩ/ (91 × 4 = 364 ) እና የሚመሯቸው እያንዳንዳቸው ሰባት ሰባት ከዋክብት አሏቸው /ሰባት ቀን የሚያበሩ/ (4 × 7 = 28) ፤ ኻያ ስምንት ከዋክብት በእየዐሥራ ሦስት (28 × 13 = 364) ቀን የሚወጡ /ለዐሥራ ሦስት ቀን የሚያበሩ/፤ በእየወሩ የሚወጡ 12 ከዋክብት /አንድ ወር ቆይተው የሚጠፉ / ፤ በእየዕለቱ የሚወጡ አንድ ሺ ከዋክብት (364 × 1000 = 364000) ወዘተ በሚል የዑደት ሥርዓት እንዳላቸው የባሕረ ሐሳብ ትምህርት በስፋት ያስረዳል።

በባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት ዘንድ ለሦስት ወር በሚቆዩት ከዋክብት ተከትለው የሚወጡ ከዋክብት አንድ አንድ ወር የሚያበሩ ከዋክብት እና ዐሥራ ሦስት ቀን የሚያበሩ ከዋክብትን ከሰው ልጅ ጋር ስለአላቸው ግንኙነት ያስተምራሉ። እንዲኹም በእየወሩ የሚወጡት ከዋክብት ከሚወጡበት ወቅት ጋር በማገናኘት የከዋክብት ባሕርያቸው ምን እንደኾነ ይናገራሉ።

ሠንጠረዥ 2፡ የፀሐይና የ12ቱ መገብተ አውራኀ ከዋክብት ባሕርይና ግብር እንደሚከተለው መደብ ሊገለጽ ይችላል።[181]

[180] መዝሙረ ዳዊት አንድምታ
[181] አለቃ ያሬድ ፤ 2004 ዓ.ም.

| ባሕርይ | ኮከብ እና የሚወጡበት ቀን | ኮከብ እና የሚወጡበት ቀን | ኮከብ እና የሚወጡበት ቀን |
|---|---|---|---|
| እሳት | ሐመል (መጋቢት 17 ቀን) - 30 ዕለት 43 ኬክሮስ | አሰድ (ሐምሌ 21 ቀን) - 31 ዕለት ከ 10 ኬክሮስ | ቀውስ (ኅዳር 16 ቀን) - 29 ዕለት ከ28 ኬክሮስ |
| መሬት | ተውር /ሠውር) (ሚያዝያ 18 ቀን) - 30 ዕለት ከ 12 ኬክሮስ | ሰንቡላ (ነሐሴ 21 ቀን) -30 ዕለት ከ42 ኬክሮስ | ጀደይ / ጀዲ ( ታኅሣሥ 17 ቀን) - 29 ዕለት 23 ኬክሮስ |
| ነፋስ | ጀውዛ/ ገውዝ (ግንቦት 17 ቀን) - 31 ዕለት ከ 30 ኬክሮስ | ሚዛን (መስከረም 17 ቀን) - 30 ዕለት ከ 10 ኬክሮስ | ደለው /ደላዊ (ጥር 17 ቀን) - 30 ዕለት ከ41 ኬክሮስ |
| ውኃ | ሸርጣን (ሠኔ 19 ቀን) - 31 ዕለት ከ 26 ኬክሮስ | አቅራብ (ጥቅምት 17 ቀን) - 29 ዕለት 40 ኬክሮስ | ሑት (የካቲት 16 ቀን) - 30 ዕለት ከ10 ኬክሮስ |

በኢትዮጵያዊያን የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት የሚያስተምሯቸው የከዋክብት ስሞች ሄኖክ ምዕራፍ 28 ከተጠቀሱት ይለያዩ። ለምሳሌ ከመስከረም 25 እስከ ታኅሣሥ 25 ድረስ ባሉት ሦስት ወራት የሚወጡ አድርናኤል፣ ኢየሱሳኤልና ኢይሉማኤልም ናቸው ይላል። በዚኽ ሠንጠረዥ ደግሞ ሚዛን አቅራብ እና ጀዲ ይላል።[182] ልዩነቱ እንዴትና ለምን እንደመጣ ግልፅ በኾነ ምክንያት ለማስረዳት በዚኽ ጥናት ማግኘት አልተቻለም።

በኢትዮጵያዊያን የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት ትምህርት መሠረት ከዋክብት የሚወጡባቸው ሰዓትና አቅጣጫም እንደሚታወቅ ይናገራሉ ። ለምሳሌ ***ሸርጣን*** የሚባለው ኮከብ ከ 3 ኮከቦች ጋር በምሥራቅ በኩል በዶሮ ጩኸት (ሌሊት በ9 ሰዓት) ይወጣል ፤ ***ሰንቡላ*** የሚባለው ኮከብ ከ 2 ኮከቦች ጋር በምዕራብ በኩል ሌሊት

[182] አለቃ ያሬድ ፈንታ፡ 2004 ዓ.ም.

7 ሰዓት ይወጣል፤ ***ሚዛን*** የሚባለው ኮከብ በዐዜብ በኩል በመንፈቀ ሌሊት (ከሌሊቱ በ6 ሰዓት) ይወጣል፡፡

## ቋሚ የመውጫ ቀን የሌላቸው ክዋክብት

ቋሚ የመውጫ ቀን የሌላቸው ስንል ዑደታቸው ዘመንን ለመቁጠር የማንጠቀምባቸው እና ሲወጡም ከተለያዩ ነገሮች ጋር የሚያያዙ ከዋክብትን ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲወለድ ነገሥታት (ሰብአ ሰገል) እጅ መንሻ ይዘው ሲኼዱ ይመራቸው የነበረ የተለየ እና የታወቀ ኮከብ እንደነበር ተገልጿል፡፡ (ማቴዎስ ወንጌል) ይኽ ኮከብ አስቀድሞ በነቢያት መሲሕ ሲወለድ የሚታዩ ከዋክብትን ምልክት ተናግረው ስለነበረ ይኽንኑ ይዘው ኮከቡን ሲያዩ እርሱን እየተከተሉ ጌታ ከተወለደበት በረት ደርሰዋል፡፡ ስለዚኽ እንዲኽ ዓይነቶቹ ከዋክብት በኢትዮጵውያን ዘንድ ከትንቢት መፈጸም እና ከተአምራት ጋር ይያያዛሉ፡፡

ለምሳሌ፡- «በውኑ የሰባቱን ከዋክብት ዘለላ ታስር ዘንድ፥ ወይስ ኦሪዮን የሚባለውን ኮከብ ትፈታ ዘንድ ትችላለህን? ወይስ ማዛሮት የሚባሉትን ከዋክብት በጊዜያቸው ታወጣ ዘንድ፥ ወይስ ድብ የሚባለውን (የምሽቱን) ኮከብ ከልጆቹ ጋር ትመራ ዘንድ ትችላለህን?´[183]፡፡ እንዲኹም «ሰባቱን ከዋክብትና ኦሪዮን የተባለውን ኮከብ የፈጠረውን፥ የሞትን ጥላ ወደ ንጋት የሚለውጠውን፥ ቀኑንም በሌሊት የሚያጨልመውን፥ የባሕሩንም ውኆች ጠርቶ በምድር ፊት ላይ የሚያፈስሳቸውን፥ አምባውም እንዲፈርስ በብርቱ ላይ የድንገት ጥፋት የሚያመጣውን ፈልጉ ስሙ እግዚአብሔር ነው፡፡[184]´

እንዲኹም ትኩላን[185] ከዋክብት የሚባሉት ኹልጊዜ በእየለቱ የሚወጡ ናቸው፡፡ በመጽሐፈ ሄኖክ ፡ በግብራቸው ቅንየታት[186] ብሏቸዋል ቅኑያን[187] ሲል ነው እንጂ ምን ያኽል እንደኾኑ ቍጥራቸውን አይገልጽም፡፡ እንዲኹም ሌሊቱ ሊነጋ ሲል የሚወጡ የአጥቢያ ኮከቦች አሉ፡፡

---

[183] ኢዮብ 38 ÷31--32
[184] አሞጽ 5 ÷8--9
[185] ትኩላን ማለት የተተከለ የማይንቀሳቀስ እንደማለት ነው፡፡
[186] ቀነየ፡ ገዛ ከሚለው ግሥ የተገኘ ሲኾን፡ ቅንየታት ማለት ገዥዎች የሚል ስለዚኽ የከዋክብት አለቆች እንደ ማለት ይኾናል፡፡
[187] የመጽሐፈ ሄኖክ አንድምታ ምዕራፍ 24፥7

# ከዋክብትን ለትንበያ አገልግሎት መጠቀም /astrology/

የባሕረ ሐሳብ መምህራን የከዋክብትን አወጣጥ ተከትለው የሚታዩ የተለያዩ ክስተቶችን ስለሚናገሩ፤ እነዚያን ክስተቶች ተከትለው ከዋክብት የሚታዩበትን ወቅት መሠረት አድርገው የከዋክብትን ባሕርያት በአራቱ ባሕርያት (እሳት፣ ውኃ፣ ነፋስና መሬት) አምሳል በመሰየም ከሰው አኗኗር ጋር ያላቸውን ግንኙነት ይተነብያሉ፡፡ የኮከብ ቈጠራ ትምህርት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ``ሐሳበ መናዝል`` ተብሎ ይጠራል፡፡ ሐሳበ መናዝል ማለት የከዋክብትን ጠባይና ግብር የሚገልጽ ስሌት ነው፡፡ መናዝል ማለትም የዐሥራ ሁለት ወር ከዋክብትን በእንስሳት ስም የሚጠሩ መገብተ አውራኅ ከዋክብት ናቸው፡፡[188]

ይኸም ከክርስቶስ ልደት በፊት ጀምሮ የታወቀ እና በእግዚአብሔርም ዘንድ የማይወደድ መኾኑን በትንቢተ ኢሳይያስ እንዲኽ ተገልጧል ‹‹በምክርሽ ብዛት ደክመሻል አሁንም የሰማይን ከዋክብት የሚቈጥሩ፥ ከዋክብትንም የሚመለከቱ፥ በየመባቻውም የሚመጣውን ነገር የሚናገሩ ተነሥተው ከሚመጣብሽ ነገር ያድኑሽ፡፡›› (ኢሳ. 47÷13)፡፡ ስለዚኽ መምህራኑ ይኽንን ሥራ እጅግ ይነቅፉታል፡፡ በዚኽም የተነሣ ይመስላል አኹን አኹን ‹‹መርሐ ዕውር›› ከሚባለው ክፍል ውጭ ያለውን ትምህርት በሚገባ ለማስተማር ፈቃደኛ አይደሉም፡፡

ሊቃውንቱ ከዋክብት የሚወጡበትን/የሚታዩበትን ጊዜ መነሻ በማድረግ ለኹነቶች ትንበያ በስፋት ይጠቀሙበት እንደነበር ብዙ ማሳያዎች አሉ፡፡ የከዋክብት ትንበያ የሚሰጠው በየወሩ በሚወጡ እና የወሩ አለቃ ተብለው በሚጠሩ 12 ከዋክብት ላይ ትኩረት በማድረግ ነው፡፡[189]

ለምሳሌ፡ በሚያዝያ ወር የሚወጣው ሐምል በድብ ይመስሉትና ይኽ ኮከብ ያለው ሰው ብሩህ አዕምሮ፣እጅግ ኃይለኛ፣ ደፋር፣ አንደበተ ርቱዕ ነው፡፡ በግንቦት ወር የሚወጣ ተውር/ሠውር ደግሞ በዝንጀሮ ይወክሉትና ባሕርይውን እጅግ ገራም፣ ምሥጢራዊ ባሕርይ አለው፣ ያደረገው ነገር ሁሉ አይታወቅበትም (ይኽም ኮከቡ ድብቅ ስለኾነ ነው) ይላሉ፡፡

[188] አለቃ ያሬድ ፈንታ፤ 2004 ዓ.ም
[189] ዐውደ ነገሥት

ከከዋክብት በተጨማሪ ጨረቃን በመጠቀም በእያንዳንዱ ቀን ምን እንደሚከሰት ይተነብያሉ፡፡

ለምሳሌ፦1ኛ ቀን 27 ጨረቃ፤ መንገድ ቢኼዱ ቤት ቢሠሩ፣ ነገር ቢጀምሩ መልካም ነው፡፡ ሕልም ቢያዩም በኹለት ቀን ይደርሳል፡፡ 2ኛ ቀን 28 ጨረቃ፤ ከሚስት ጋር በግብረ ሥጋ ቢገናኙ መልካም ነው፡፡የሚወለደው ልጅ ብልሕ፣ ዐዋቂ፣ ጥበበኛ፣ ተመራማሪ፣ ፈላስፋ ይሆናል፡፡ ያየው ሕልም በ 7 ቀን ይፈጸማል ይላሉ፡፡

እንዲኽ እያሉ ለሠላሳዉም ዕለት ይከሰታል፣ ይኾናል የሚሉትን ትንበያ ያስቀምጣሉ፤ በአንጻሩ ሊፈጠር ይችላል ላሉት ችግርም መፍትሔ ይኾናል የሚሉትን እንደ ጸሎትና ብዙ እንቅስቃሴዎችን በዚያ ዕለት አለማድረግ የሚሉትን ጨምሮ በስፋት ይመክራሉ፡፡[190] ይኽን የከዋክብት ጥናት ስንመለከት ባሕረ ሐሳብ ጥልቅ የኾነ የሥነ ክዋክብት (Astronomy and astrology) ትምህርት በስፋት የሚሰጥበት ጥበብ መኾኑን እንገነዘባለን፡፡

## የአየር ንብረት ትንበያ /Meteorology/

በባሕረ ሐሳብ መምህራን ዘንድ የየወቅቱ የአየር ሁኔታ በፀሐይ አካኼድና በነፋስ አቅጣጫ ይወሰናል፡፡ ቋሚና በየዓመቱ ተደጋግመው የሚከሰቱት የሙቀትና የቅዝቃዜ፣ የርጥብና የደረቅ አየር ሁኔታ፣ የዝናብና የድርቅ ወቅቶች፣ የመሳሰሉት ክስተቶች በአንድ ዓመት ውስጥ በሚለዋወጡ የፀሐይ ዑደት አቅጣጫና የነፋስ አቅጣጫ ተለይቶ ይታወቃል፡፡

## የፀሐይ ዑደትና የወቅቶች መፈራረቅ

የሙቀትና የቅዝቃዜ፣ የደረቅና የርጥብ አየር፣ እንዲኹም የክረምትና የበጋ ወቅቶች ይፈራረቃሉ፡፡ ይኽም የፀሐይን ዑደት ተከትሎ የሚሰላ ነው፡፡ ይኽ ስሌት እጅግ ቀደም ካለው የሰው ልጅ ታሪክ ጀምሮ በስፋት የሚታወቅ ሲኾን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ከቅዱስ ያሬድ ጀምሮ እያንዳንዱ ቀንና ወር ምን ዓይነት ጠባይ እንዳለው በማስታወስ ለዚያ የሚስማማ የጸሎትና የትምህርት ሥርዓት ተዘጋጅቷል፡፡[191]

190 ዝኒ ከማሁ

191 ቅዱስ ያሬድ በድጓው በዓመቱ ውስጥ ለሚመላለሱት ወቅቶች ለያንዳንዳቸው የሚስማማ ዝማሬዎችን አዘጋጅቷል፡፡

## ነፋሳት እና የአየር ንብረት

ስለአየር ኹኔታ ለመናገር  የነፋስን ጠባይና አካሔድ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ሄኖክ ስለነፋስ ሲናገር  እንደ ፀሐይና ጨረቃ ኹሉ ለነፋስም ዐሥራ ኹለት መስኮቶች እንዳሉት ይናገራል፡፡ ‹‹ነፋሳት፡ ከእነርሱ የሚወጡባቸውና በምድር ላይ የሚነፍሱባቸው ለነፋሳት ኹሉ የተከፈቱ ዐሥራ ኹለት መሰኮቶችን በምድር ዳርቻ አየሁ፡፡››[192] በዚህ በሄኖክ አገላለጽ መሠረት ነፋሳት የሚወጡት ከምድር ዳርቻ በአራቱ ማዕዘን ነው ማለት ነው፡፡

የነፋስ ባሕርይው ርጡብነት (ቅዝቃዜ)፣ ውዑይነት (ሙቀት) እና ጽሉምነት (ጥቁር/ ጨለማ) እንደኾኑ ይታመናል፡፡[193] እነዚኽ ባሕርያት የነፋስን አጠቃላይ ምንነት የሚገልጹ ናቸው፡፡ ነፋስ ዝናም እንዲዘንብ የሚያደርግ ውርጭንም የሚያመጣ እንዲኹም ሙቀት እንዲጨምር የሚያደርግ ነው፡፡[194] ሄኖክ ነፋሳት የሚነሡበትን አቅጣጫ መነሻ አድርጎ እንደ ከዋክብት በስም ጠርቷቸዋል፡፡ ሄኖክ በዐሥራ ኹለት መሰኮቶች የሚወጡ ዐሥራ ኹለት ነፍሳት አሉ እነዚኽም አራቱ ነፋሳተ ምሕረት እና ስምንቱ ነፋሳተ መዓት ናቸው፡፡ የእነዚኽንም ነፋሳት የእያንዳንቸውን ባሕርይና ግብር እንዲኹም የሚወጡባቸው መስኮቶቸንና ጊዜአቸውን በዝርዝር በመግለጽ ለልጁ ለማቱሳላ አስተምሮታል፡፡[195]

## በአራቱ  ማዕዘን የሚነፍሱ ነፋሳት

የመጀመሪያው ነፋስ  ቀዳማዊ  ስለኾነ ስሙ ጽባሐዊ ይባላል፤ በደቡባዊ ምሥራቅ አቅጣጫ ካለው አንደኛው ደጃፍ ውስጥ ይወጣል፡፡ ኹለተኛውም ነፋስ ስሙ አዜብ ይባላል፤ በሰሜን አቅጣጫ ከምትገኘው ሦስተኛው መስኮት ይወጣል፡፡ ሦስተኛው በምዕራብ የሚነፍሰውም ነፋስ ስሙን ንቱግ (የጎደለ) ይሉታል፡፡ ምክንያቱም የሰማይ ብርሃናት  ኹሉ በዚያ ሕጸጽ ስለሚያደርጉና ወደ እዚያም ስለሚገቡ ነው፡፡ ይኽ አባባል በዘመናችን የሥነ ሕዋ ምርምር ዘርፍ በአዲስ መልክ እየተጠና ካለውና በሳይንሳዊ አጠራሩ ጥቁር ቀዳዳ (Black hole) ከሚባለው ጋር ምን ግንኙነት

[192] መጽሐፈ ሄኖክ ምዕራፍ 25
[193] አክሲማሮስ ዘኤጲፋኖስ
[194] ዝኒ ከማሁ
[195] አለቃ ያሬድ ፈንታ ፤ 2004 ዓ.ም

እንዳለው የዘመናችን የዘርፉ ሊቃውንት በተለይ የሕዋ ሳይንስ አጥኝዎች ቢያገናዝቡት ጥሩ የምርምር ፍንጭ ሊሰጥ ይችላል የሚል ግምት አለን።

አራተኛው ነፋስ ስሙ መስዕ ተብሎ የሚጠራ ሲኾን በሦስት ክፍሎች ይከፈላል። እነርሱም አንደኛው የሰዎችን ማደሪያ የሚያጸና ነው። ኹለተኛውም በውኃ አካላት ላይ በባሕሮችና በቀላያት፣ በደኖችና በወንዞች፣ በጨለማና በደመናት የተሾመ ነው። ሦስተኛው በቸርነቱና በምሕረቱ በምትወረስ በገነት ጽድቅ ላይ የተሾመ ነው።

የደቡብ ነፋሳት ከሦስት ደጃፎች ውስጥ ይወጣል። ከእነርሱም በምሥራቅ አቅጣጫ ከምትገኘው ከአንደኛይቱ ደጃፍ ውስጥ የሞቀ ነፋስ ይወጣል። ከዚኽ ደጃፍ አጠገብ ካለችው ከመካከለኛይቱ ደጃፍ በጎ ሽቶ፣ ጠልና ዝናብ፣ ሰላምና ሕይወት ይወጣሉ። የሰሜን ነፋሳት በአሉበት በምሥራቅ ከምትገኘው ከሰባተኛው ደጃፍ ጠልና ዝናብ፣ ኲብኲባና ድምሳሴ ይወጣሉ። ከመካከለኛይቱ ደጃፍ ቀጥተኛ በኾነ መንገድ ዝናብና ጠል ሕይወትና ሰላም ይወጣሉ በማለት በመጽሐፈ ሄኖክ ተገልጿል።

## የ፲ሥራ ኹለቱ ነፋሳት መስኮቶች

በመጽሐፈ ሄኖክ ምዕራፍ 24 መሠረት በማድረግ በእየወሩ የሚወጡ ነፋሳትና ምልክቶቹ እንደሚከተለው ያቀርባል በ 1ኛ ደጃፍ የሚወጣው ነፋስ ስሙ ጽባሕይ ሲባል በምሥራቅ ግራ ካለችው መስኮት ይወጣል። ይኽ ነፋስ በወርኃ ጥቅምት በሚወጣበት ጊዜ ጥፋት፣ ድርቅ እና ጉዳት ይኾናል። በ 2ኛው ደጃፍ የሚወጣው ነፋስ በምሥራቅ መካከል ካለችው መስኮት በወርኃ ኅዳር ሲወጣ ቅን ሥራ፣ ዝናም፣ ፍሬ፣ ጤዛና ሕይወት ይወጣሉ። በ 3ኛው ደጃፍ የሚወጣው ነፋስ በምሥራቅ ቀኝ ካለችው መስኮት በወርኃ ታኅሣሥ ብርድ፣ ውርጭ፣ ድርቅና ዋግ ይወጣሉ። በ4 ኛው ደጃፍ የሚወጣው ነፋስ በደቡብ ቀኝ ካለችው መስኮት በወርኃ ሚያዝያ የሚሞቅ ነፋስ፣ ድርቅ፣ ጥፋትና ጉዳት ይወጣል። በ5ኛው ደጃፍ የሚወጣው ነፋስ በደቡብ መካከል ካለችው መስኮት በወርኃ ግንቦት መልካም ሽታ፣ ጤዛ፣ ዝንም፣ ፍቅርና ጤና ይወጣል። በ 6ኛው ደጃፍ የሚወጣው ነፋስ በደቡብ ግራ ካለችው መስኮት በወርኃ ሠኔ ጤዛ፣ ዝናም፣ አንበጣና ጥፋት ይወጣል። በ 7ኛው ደጃፍ የሚወጣው ነፋስ በሰሜን ቀኝ ካለችው መስኮት በወርኃ ሐምሌ ጉም፣ ውርጭ፣ ዋግ፣ ዝናም፣ ጤዛና አንበጣ ይወጣል። በ 8ኛው ደጃፍ የሚወጣው ነፋስ በሰሜን መካከለኛ ካለችው መስኮት በወርኃ ነሐሴ ቅን ነገር፣ ሕይወት፣ ዝናም ፣ ጤዛና ፍቅር ይወጣል። በ 9ኛው ደጃፍ የሚወጣው ነፋስ በሰሜን ግራ ካለችው መስኮት በወርኃ መስከረም

ጤዛ፣ ዝናም፣ አንበጣና ጥፋት ይወጣል። በ 10ኛው ደጃፍ የሚወጣው ነፋስ በምዕራብ ግራ ካለችው መስኮት በወርኃ ጥር ጤዛ፣ ውርጭ፣ ብርድ፣ ዋግና ቀጭ ይወጣል። በ 11ኛው ደጃፍ የሚወጣው ነፋስ በምዕራብ መካከል ካለችው መስኮት በወርኃ የካቲት ጤዛ፣ ዝናም፣ በረከትና ሰላም ይወጣል። በ 12ኛው ደጃፍ የሚወጣው ነፋስ በምዕራብ ቀኝ ካለችው መስኮት በወርኃ መጋቢት ድርቅ፣ ጥፋት፣ መቃጠልና ጉዳት ይወጣል።[196]

እንዲኹም የነፋሳት አቅጣጫ በሀገርና በሰው ሕይወት ላይ የሚመጡ ክስተቶች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳለው ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ያስተምራሉ። የነፋሱን አካኼድ ተመልክተውም በሀገሪቱ ላይ የሚመጡ እንደ ጦርነት፣ ድርቅ፣ ቸነፈር ወዘተ መቼ ሊከሰት እንደሚችል ወቅቱን (ጊዜውን) ለይተው ይናገራሉ። ከዚኽ በመነሣት ባሕረ ሐሳብ የነፋሳትን ባሕርይ በማጥናት ከሰው ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማጥናት እንደሚቻል እና ለአየር ንብረትና የአየር ጠባይ (climate and weather studies) ምርምርን መረዳት የሚያስችል ጥብብ በውስጡ የያዘ ነው።

## ማጠቃለያ

በምዕራባውያን ሊቃውንት ዘንድ አሁንም ከጥንታዊዉ የሕዋ ሳይንስ ትምህርት ጋር በማገናዘብ የኢትዮጵያውያን ስሌት (በተለይ ከመጽሐፈ ሄኖክ መተዋወቅ ጋር ተያይዞ) በስፋት እየተጠና ይገኛል። በዚኽም ጥናት ከላይ በዝርዝር እንደተገለጸው መጽሐፈ ሄኖክ ለባሕረ ሐሳብ፣ ለዘመን አቈጣጠር እና ለአየር ትንበያ ዕውቀት መሠረትና የጥናት መነሻ መኾኑን ለማየት ተችሏል።

ባሕረ ሐሳብ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ተወዳጅና መጠነ ሰፊ ጥቅም ያለው ጥበብ ነው። ኢትዮጵያ ዘመን መቍጠር የጀመረችው ከክርስቶስ ልደት በፊት ምን አልባትም ከሄኖክ ዘመን ጀምራ መኾኑን በዚኽ ጥናት ተገልጿል። ባሕረ ሐሳብ የኢትዮጵያ የዘመን አቈጣጠር ስልት በአንድ ጊዜ በፀሐይ፣ በጨረቃና በከዋክብት እንደ አስፈላጊነታቸው መቍጠር ስለሚያስችል ልዩ ያደርገዋል። እንዲኹም አጽዋማትን፣ በዓላትንና የጸሎት ጊዜያትን ለይቶ በማውጣት ሕዝቡ ለመንፈሳዊ ተግባራት እንዲጠቀምበት። ይኽም ልዩ እና የራሱ አሠራር ቅደም ተከተል (Algorithm) ያለው ጥበብ መኾኑን መረዳት ያስፈልጋል።

[196] ዝኒ ከማሁ

ባሕረ ሐሳብ በመጽሐፈ ሄኖክ በተለይ ከምዕራፍ 21 እስከ 28 መነሻ ባደረገ መልኩ የተዘጋጀ እንደኾነ ለመረዳት ተችሏል። ይኽንንም መነሻ በማድረግና በጥልቀት በመመርመር የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት መቼ እንደሚወጡ እና ሲወጡ የሚታዩ ምልክቶችን እንዲኹም የአንዳንዶችን ለምን እንደሚወጡ አስረግጠው ይናገራሉ። የነፋስ አቅጣጫ በመለየት ምን ሊከሰት እንደሚችል ይተነብያሉ። ስለዚኽ ቀደም ባሉት ዘመናት ባሕረ ሐሳብ በኢትዮጵያ ብዙ ጥቅም ሲሰጥ ቆይቷል። በዘመን አቈጣጠር፣ የሰማይና የምድርን የፈለክ ፈለካት ‹‹ምሥጢር›› ለማወቅ (astronomical studies)፣ ለኮከብ ቈጠራ (astrology)፣ ለአየር ንብረት ትንበያና ስለወቅቶች መፈራረቅ (meteorology and climate studies) ለመሳሰሉት ጉዳዮች ኹሉ በማኅበረሰቡ ዘንድ በሰፊው አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል። የባሕረ ሐሳብ ትምህርት ከሄኖክ መጽሐፍ በተጨማሪም በጊዜ ኺደት ለማብራራት የተጨመሩ አገላለጽ እንዳለ በዚኽ ጥናት ተዳሷል።

የባሕረ ሐሳብ ትምህርት በዘመናዊ ሳይንስ ከፍተኛ የሒሳብ (Mathemathics) እና የሕዋ ዕውቀት እና የምርምር ችሎታ የሚጠይቀውን ትምህርት በቃል ብቻ በፍጥነት ያለ ጽሑፍ ወይም ያለ ሒሳብ መሣሪያ ማሽን መሥራት እንደሚቻል የሚያሳይ ሀገር በቀል ጥበብ ነው። የትምህርት አሰጣጡም በመጽሐፍ ሄኖክ እንደተገለጸው በቀላሉ ለማስታወስ እንዲቻል በምልክት እና በቅደም ተከተል(Algorithm) ከቀላል ወደ ከባድ የሚኼድ ሥርዓት ያለው እና የተማሪዎችን በኹሉም መንገድ የሚያሳትፍና የሚያበረታታ ነው።